# <u>የመጽሐፍ ትችት</u>

*መሓሪ ረዳኢ፣ የተሸሻለውን የቤተሠብ ህግ ለመገንዘብ የሚረዱ አንዳንድ ነጥቦች፣ ቅጽ አንድ፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 1995 ዓ.ም. 189 ገጽ ብር 25*

ማርታ በለጠ*

ቤተሰብ የአንድ ማህበረሰብ ዋና አካል ሲሆን ለዚህ አካል ሊሰጥ የሚገባውን ጥበቃ አብዛኞች ሀገሮች በህጎቻቸው ይደነግጋሉ፡፡ ወደ ሀገራችንም በምንመጣት ጊዜ የቤተሰብ ጉዳይ ከፍትሃ ነገስት ጊዜ ጀምሮ በተለያዩ ህጎች ከለላና ጥበቃ ሲደረግለት ቆይቷል፡፡ በ1952 ዓ.ም. በሥራ ላይ የዋለውም የፍትሐ ብሔር ህግ ለቤተሰብ ጥበቃና ከለላ በማድረግ ለረጅም ጊዜ ሲያገለግል ቆይቷል፡፡ በአንዳንድ ክልሎች አሁንም ድረስ በማገልገል ላይ ይገኛል፡፡ ሆኖም ግን አንዳንድ በህጉ ውስጥ የሚገኙ አንቀጾች ኢትዮጵያ ካፀደቀቻቸው አለም አቀፍ ስምምነቶች እንዲሁም ከ1987 ዓ.ም. ጀምሮ በሥራ ላይ ከዋለው የአገሪቱ ህገ መንግስት ጋር የሚቃረን በመሆኑ እንዲሁም ደግሞ ህጉ አሁን ማህበረሰቡ ከደረሰበት የእድገትና የአስተሳሰብ ለውጥ ጋር አብሮ የማይሄድ በመሆኑ ህጉን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም የፌዴራሉ የህግ አውጪ አካል በ1992 ዓ.ም. የተሻሻለውን የቤተሰብ ህግ አጽድቆ ተግባራዊ አድርጓል፡፡

በዚህ ጽሁፍ ለመዳሰስ የሚሞከረውም መጽሃፍ ይህንን በቤተሰብ ህጉ ዙሪያ የተደረገውን አዲስ ለውጦች በመመርኮዝ አንዳንድ ማብራሪያዎችን የሰጠ ሲሆን የጽሃፉም አዘጋጅ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የህግ ፋኩልቲ በመምህርነት እንዲሁም በፍትህና የህግ ስርአት ምርምር ኢንስቲትዩት ስር በተቋቋሙት የፌዴራል ህጎች ማሻሻያ የስራ ቡድኖች የቤተስብ ህግ ባረቀቀው ኮሚቴ ውስጥ በአባልነት ያገለገሉ ናቸው፡፡

መጽሐፉ በስድስት ምዕራፎች የተከፋፈለ ሲሆን ከመግቢያው ለመረዳት እንደሚቻለው የመጽሐፉ ዋና ዓላማ በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ዙሪያ ለግንዛቤ የሚረዱ ነጥቦችን ለመጠቆም እንዲሁም በአገሪቱ ህግ ላይ የተፃፉ ማብራሪያዎችና ትችቶችም ጥቂት በመሆናቸው በዚህ ህግ ዙሪያ ትችት ለመስጠትና ለመነሻ የሚሆኑ ሃሳቦችን ለማቅረብ ነው፡፡ የመጀመሪያው ምዕራፍ የአዋጁን ቅርጽ በተመለከተ በነጠላ አዋጅነት መልክ የወጣበትን ምክንያት የአዋጁ ተፈጻሚነት በአዲስ አበባ እና በድሬዳዋ ከተሞች ብቻ የተወሰነ መሆኑን እንዲሁም የአዋጁን ይዘት ከፍትሃ ብሄር ህጉ ጋር በማነጻጸር ያብራራል፡፡ ወደ ሁለተኛው ምዕራፍ በመንንመጣበት ጊዜ የጋብቻ አፈደፃፀም ስርዓቶች ዓይነትና ሊሟሉ የሚገባቸው በሕጉ የተገነገኑ ሁኔታዎችን የሚያብራራ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ጋብቻ በተጋቢዎች መካከል የሚፈጥረው ግላዊና በገንዘብ በኩል የሚኖረው ውጤት በሦስተኛው ምዕራፍ የተብራራ ሲሆን ቀጣዩ ምዕራፍ ጋብቻ ለማፍረስ ምክንያት የሚሆኑት በሕጉ የተቀመጡትን ሁኔታዎች እንዲሁም የጋብቻው መፍረስ የሚያከትለውን ውጤት ያትታል፡፡ መጽሐፉ ጋብቻ ለመፈጸሙ ለማስረዳት ስለሚቀርቡ ማስረጃዎች ምንነት እንዲሁም ሕጉ ጋብቻ

---

*በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የህግ ፋኩልቲ መምህር

ሳይፈጸም እንደ ባልና ሚስት አብረው ለሚኖሩ ሰዎች የሰጠውን ከለላ በማብራራት ያበቃል፡፡

መጽሐፉ ለህግ ተማሪዎች፣ ባለሙያዎችና በቤተሰብ ህግ ዙሪያ ጥናት ማድረግ ለሚፈልጉ ሰዎች ሊያገለግል ይችላል፡፡ እንዲሁም መጽሐፉ በአማርኛ መፃፉ የተጠቃሚዎችን ቁጥር ከማስፋቱም በተጨማሪ መጽሐፍ ቀለል ባለ አቀራረብና ቋንቋ በመዘጋጀቱ ይዘቱን ለመረዳትም የህግ ባለሙያ መሆን የግድ አይልም፡፡

በመጽሐፉ ውስጥ ለመንደርደሪያነት የሚያገለግሉ ነጥቦች የተካተቱ ሲሆን የተሻሻለው ህግ በሚወጣበት ወቅት የነበሩትን ከተለያዩ የማኅበረሰቡ አካሎች ይንፀባረቁ የነበሩትን ሃሳቦች ጠቅለል ባለ መልኩ መያዙ በህጉ ዙሪያ ለሚደረጉ ጥናቶች ጠቃሚነት ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም የህግ ትርጓሜ በሚያስፈልግባቸው ጊዚያቶች የህግ አውጪው ዓላማ ምን እንደነበረ ለማስገንዘብ ይረዳል፡፡ ከፍትሐ ብሔር ህጉ ለውጥ የተደረገባቸው አንቀጾችና ምክንያታቸው መቅረቡ ለዚህ ተግባር አጋዥ ይሆናል፡፡

በአጠቃላይ መጽሐፉ ከላይ የተገለፁት ጥቅሞች ሲኖሩት አንዳንድ መሻሻል ሊደረግባቸው የሚገባ ነጥቦችም ይኖራሉ፡፡ በዚህ ረገድ የመጽሐፉን ቅርፅ በምንመለከትበት ጊዜ ስለጋብቻ ምዝገባ የሚደነግገው የህጉ ክፍል እና ጋብቻን ለማስረዳት ስለሚቀርቡ ማስረጃዎች በተመለከተ በተለያየ ክፍል ተፅፈው እናገኛቸዋለን፡፡ በዋነኛነት ጋብቻን ለማስረዳት የሚቀርበው ማስረጃ የጋብቻ ምስክር ወረቀት ሲሆን ይህ ደግሞ ጋብቻን ከማስመዝገብ ግዴታ ጋር ተያይዞ የሚታይ ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም በመጽሐፉ ክፍል 2.4. እና በምዕራፍ አምስት የቀረቡት ሃሳቦች ተነጣጥለው የማይታዩ ስለሆኑ በሚቀጥለው ዕትም ላይ በአንድ ክፍል እንዲቀርቡ ቢደረግ መልካም ነው፡፡

ወደ ይዘቱ በምንገባበት ጊዜ የሁለተኛው ምዕራፍ የጋብቻ አፈፃፀም ስርዓት አይነቶችንና ጋብቻ ሲፈፀም ሊሟሉ የሚገባቸውን በህጉ የተደነገጉ ሁኔታዎችን የሚያብራራ ሆኖ እናገኘዋለን እንዲሁም ደግሞ በሌሎች ሀገሩ ህጎች ጋብቻ የሚለው ቃል የተሠጠውን ትርጓሜ ሲያቀርብ የኢትዮጵያ ህግ ለቃሉ ትርጓሜ ያልሰጠበትንም ምክንያት ያቀርባል፡፡ ሆኖም ግን መጽሐፉ ለተለያዩ የማኅበረሰቡ ክፍሎች የህግ ተማሪዎችን ጨምሮ አገልግሎት እንዲሰጥ የታሰበ ከመሆኑ አንፃር ከተለያዩ የህጉ አንቀጾች በመነሳት ጋብቻ ምን ተብሎ ሊተረጎም እንደሚችል የናሙና ትርጓሜ ቢሰጥ መልካም ይሆናል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በገጽ 45 የግርጌ ፅሁፍ 39 በማታለል የተፈፀመን ጋብቻ የቤተሰብ ህጉ የማያካትት ቢሆንም በስህተት የተፈፀመ ጋብቻ የሚለው ስር ይወድቃል የሚል አስተያየት በጸሐፊው ተሰጥቶአል፡፡ ነገር ግን ስህተት እና ማታለል (Mistake and Fraud) የተለያየ ትርጓሜ የሚሰጣቸው ሃሳቦች ሲሆኑ የሚፈለግባቸውም የአዕምሮ ሁኔታ የተለያየ ነው፡፡ በተጨማሪ በዚህ መልኩ ህጉን መተርጎም የህግ አውጪው አካል ለጋብቻ መፈፀም እንደቅድመ ሁኔታ ካስቀመጣቸው መስፈርቶች ተጨማሪ መስፈርት ማስቀመጥ ይሆናል፡፡

በሌላ መልኩ መጽሐፉ በገጽ 30 ጋብችን ለመፈፀም መሟላት ካለባቸው ሁኔታዎች አንዱ ስለሆነው በብቸኝነት ለመኖር የተወሰነ ጊዜ ያወሳል፡፡ ይህን ቅድመ ሁኔታ በተመለከተ ዓላማው ከልጆች ማንነታቸውን የማወቅ መብት አንፃር መታየት ያለበት መሆኑን እና በሴቶች አላግባብ የሆነ ተፅእኖ ለማሳደር አለመሆኑን አትኩሮት ተሰጥቶ ተገልጿል፡፡ ይህ ደግሞ በአንድ አንድ ወገኖች የሚነሳውን ክርክር በጥሩ መልኩ የሚመልስ በመሆኑ ተገቢነት ያለው ነው፡፡

መፅሐፉ ጥሩ የሆነ የመንደርደሪያ ነጥቦችን ያቀረበና የህጉን አወጣጥ ታሪካዊ ሂደት የሚያሳይ ቢሆንም በዳሳሹ እይታ የመፅሐፉ ዋና ድክመት የሚጠበቀውን ያህል ትችት ይዞ አለመገኘቱ ነው፡፡ ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው የመጽሐፉ አንደኛው ዓላማ በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ዙሪያ ትችቶችን መስጠት ነው፡፡ ነገር ግን ይህ ዓላማው በመጽሐፉ ውስጥ በበቂ ሁኔታ ሲንፀባረቅ አይስተዋልም፡፡

በአጠቃላይ በአገሪቷ ህግ ዙሪያ የተጻፉ ማብራሪያዎችና ትችቶች በአብዛኛው ካለመኖሩ አንጻር የዚህ መጽሃፍ መጻፍ በጣም ጥሩ ጅምር ነው፡፡ እንዲሁም ደግሞ በምጽሃፉ ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉትን የህብረተሰቡን ክፍሎች በምንመለከትበት ጊዜ የመጽሃፉን ሚና ያጎላዋል፡፡